ውድነሽ ፡ ከማጀት ፡ በሰፌ ፡ ዋንጫ ፡ ጠላ ፡ ይዘው ፡ መጡና ፡ እባላቸው ፡ ፊት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፉት ፡ ብለው ፡ - " እንካ ፡ ባይጥምም ፡ ጥም ፡ ይቆርጣል ።" አሉ ፡ ትንሽ ፡ እንደመሳቅ ብለው ። እመት ፡ ውድነሽ ፡ ትንሽ ፡ እንደመሳቅ ፡ ሲሉ ፡ የሚ ስደነግጥ ፡ ልዩ ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ነበራቸው ። አቶ ፡ ቦጋለ ፡ ተቀ ለው ፡ አንድ ፡ ጉንጭ ፡ ዋጡና ፡ ምሽታቸው ፡ ወደምጣዳቸው ፡ መሄድ ፡ ሲጀምሩ ፦

"ውዴ ፡" አሉ ። እመት ፡ ውድነሽ ፡ ዘወር ፡ ቢሉ ፡ ያቶ ፡ ቦጋለ ፡ ከንፈሮች ፡ ዘርዘር ፡ ያሉ ፡ ውብ ፡ ጥርሶቻቸውን ፡ ትተው ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሸሽ ፡ ብለው ፡ ፊታ ቸውና ፡ አይኖቻቸው ፡ ነውሩ ፡ እንደተገለጸበት ፡ ሰው ፡ ትንሽ የፍረት ፡ ቀለም ፡ ቀባ ፡ አድርጎዋቸው ፡ አዩ ። እመት ፡ ውድ ነሽ ፡ ይህ ፡ አይነት ፡ አጠራርና ፡ ይህ ፡ አይነት ፡ አስተ የት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ መሆኑን ፡ ስለሚያውቁ ፡ ተመልሰው ፡ ወደባላቸው ፡ እዩሄዱ ፡ "ምነው ?" አሉ ። የሳቸውም ፡ ፊት ፡ ለልባቸው ፡ የተሰማውን ፡ የፍቅርና ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ እንደ ፡ ንጹህ ፡ መስትዋት ፡ አጥርቶ ፡ እያሳዩ ። የሳቸውም ፡ አይኖች ፡ እንደ ፡ ነውረኛ ፡ አይን ፡ የሚያርፉበት ፡ ጠፍቶዋ ቸው ፡ ይንከራተቱ ፡ ነበር ። እመት ፡ ውድነሽ ፡ ሀብታቸው ፡ ሲጠፋ ፡ በድህነታቸውና ፡ በችግራቸው ፡ ጊዜ ፡ እንኩዋ ፡ በሁ ዋላ ፡ እድሜ ፡ እስኪወስድባቸው ፡ ድረስ ፡ ውበታቸውና ፡ ደም ፡ ግባታቸው ፡ አልተለዩዋቸውም ። አቶ ፡ ቦጋለ ፡ የምሽ ታቸውን ፡ ቀኝ ፡ እጅ ፡ ይዘው ፡ ትንሽ ፡ ሳብ ፡ ሲያደርጉዋ ቸው ፡ እቅፋቸው ፡ ላይ ፡ ወደቁ ፤ ወዲያው ፡ ከንፈሮቻቸው ፡ ተገናኙ ።

" እምጣዱ ፡ ላይ ፡ እንጀራ ፡ አለ ፤ ያራል ፡ ! " አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ራሳቸውን ፡ እባላቸው ፡ ደረት ፡ ላይ ፡ ዛል ፡ አድርገው ፡ እንደጣሉ ፡ ሽቅብ ፡ አይናቸውን ፡ እያዩ ።

" ይረር ፡ ምናባቱ ! " አሉ ፡ ባልዮው ፤ እኒያ ፡ እደረታ ቸው ፡ ላይ ፡ የወደቁት ፡ ውብ ፡ ወይዘሮ ፡ የሳቸው ፡ እንዳል ሆኑና ፡ የሂዱ ፡ እንደሆነ ፡ አይመለሱም ፡ ብለው ፡ እንደፈሩ ፡ ሁሉ ፡ እቅፋታቸውን ፡ ጠበቅ ፡ እያደረጉ ። በሁዋላ ፡ እመት ፡



ውድነሽ ፡ ተነስተው ፡ ወደምጣዱ ፡ ሲሄዱ ፦

" አባባ ፡ እምጄ ! " አለ ፡ በዛብህ ፡ ከንፈሩን ፡ አፌዞ ። እኔንም ፡ እንደማማ ፡ ሳመኝ ፡ ማለቱ ፡ ነው ። ከዚያ ፡ አቶ ፡ ቦጋለ ፡ እዬሳቁ ፡ ከተቀመጡበት ፡ አንስተው ፡ ታቅፈው ፡ እናቱን ፡ በሳሙበት ፡ አፋቸው ፡ ደጋግመው ፡ ሳሙት ።

" አየ ፡ አያ ፡ ቦጋለ ! አየ ፡ አያ ፡ ቦጋለ ! የምትሰራው ፡ ስራ ! " አሉ ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ሙግዱን ፡ ከምጣዱ ፡ ላይ ፡ ሲያነሱ ፤ እንጀራው ፡ ያረረ ፡ አያ ፡ ቦጋለ ፡ ብቻቸውን ፡ በሰ ሩት ፡ ስራ ፡ እንደሆነ ፡ ሁሉ ።

" አረረ ? " አሉ ፡ ባልዮው ።

" አረረ ፡ ትላለህ ? ከሰል ፡ ሆነ ፡ እንጂ ! "

" ተዪው ፡ ይረር ፡ ምናባቱ ! "

" እሱስ ፡ ግድየለም ፡ ምጣዱ ፡ እንዳይበላሽ ፡ ነው ፡ እንጂ ! "

" ለምን ፡ ይበላሻል ? "

" ምጣድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በላዩ ፡ እንጀራ ፡ ካረረ ፡ ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ እንጀራ ፡ ተበላሽቶ ፡ ነው ፡ ደህና ፡ ማውጣት ፡ የሚቻል ። "

" ታዲያ ፡ ይሁና ! "

" እንዲያውስ ፡ ወደን ፡ ነው ? "

እመት ፡ ውድነሽና ፡ አቶ ፡ ቦጋለ ፡ በጣም ፡ የሚዋደዱ ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ ነበሩ ። ብቻ ፡ የተወለዱበት ፡ ያደጉበትና ፡ የኖሩበት ፡ ሁኔታ ፡ የተለያዩ ፡ ስለነበረ ፡ ይልቁንም ፡ መጀ መሪያ ፡ እንደተጋቡ ፡ በመሀከላቸው ፡ የነበረው ፡ ግጭትና ፡ ኩርፊያ ፡ ይበዛ ፡ ነበር ። ደግነቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ ኩርፊያውን ፡ ተከትሎ ፡ የሚመጣው ፡ አዲስ ፡ ፍቅር ፡ ስለነበረ ፡ ግጭቱና ፡ ኩርፊያው ፡ የቂም ፡ መታሰቢያ ፡ ሳይተው ፡ ያልፍ ፡ ነበር ። በሚዋደዱ ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ መሀከል ፡ የሚነሳ ፡ ግጭት ፡ እሌስ ፡ ፍቅር ፡ ፈጥሮ ፡ ባልና ፡ ምሽቱን ፡ የበለጠ ፡ እንደሚ ያዋድድ ፡ በማይዋደዱ ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ መሀከል ፡ የሚነሳ ፡ ግጭት ፡ ግን ፡ በቂም ፡ ላይ ፡ ቂም ፡ ጨምሮ ፡ ወደመለያዬት ፡ እንደሚያደርስ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

አንድ ፡ ሰአት ፡ እንኩዋ ፡ አብሮዋቸው ፡ ለመቆዬት ፡ ፈራ ። ስለ ዚህ ፡ ያኑለት ፡ ተሰናብቶ ፡ ወደ ፡ ዲማ ፡ ተጉዋዘ ።

## ምእራፍ ፡ ፰ ፡

## የቅኔ ፡ ማእበል ፡

በዛብህ ፡ ዲማን ፡ ከወሬው ፡ በቀር ፡ ረግጦት ፡ አያውቅም፡ ነበር ። ዲማ ፡ በጎጃም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ካላቸው ፡ አድባራት ፡ አንዱ ፡ በመሆኑ ፡ እንደስሙ ፡ መልኩ ፡ ያማረ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ተሰርቶ ፡ በዙሪያ ፡ ገባው ፡ ያሉትን ፡ አገሮች ፡ ዘቅዝቆ ፡ የሚያይ ፡ ከተማው ፡ የሞቀ ፡ የደመቀ ፡ ህዝቡ ፡የሰለጠነ ፡ መስሎ ፡ ይታየው ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ገናና ፡ ደብር ፡ መቼ ፡ ደርሼ ፡ አይቼው ፡ እያለ ፡ ሲሄድ ፡ ወደአንድ ፡ ትንሽ ፡ ኮረብታ ፡ ደረሰና ፡ እሰዋን ፡ እንደ ፡ ዞረ ፡ እደልዳላ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ መንደር ፡ አዬ ። ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ እማሀል ፡ በዙሪያው ፡ የመንደሩ ፡ ቤቶች ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ችፍግ ፡ ብለው ፡ ሚጡቶችዋ ፡ የከበቡዋት ፡ዶሮ ፡ ይመስላል ። ከመንደሩ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ዙርያ ፡ ገባው ፡ በገብስ ፡ ሰብል ፡ በስንዴና ፡ በሽንብራ ፡ በጤፍም ፡ ቡቃያ ፡ ተዠጎርጉሮ ፡ አጊጦዋል ። መንደሩ ፡ ብቻ ፡ እንደተቃጠለ ፡ ሁሉ ፡ ከአመድ ፡ ክምር ፡ በቀር ፡ እርጥብ ፡ ነገር ፡ አይታይበትም ።

በዛብህ ፡ ገና ፡ እመንደሩ ፡ ሳይደርስ ፡ አንድ ፡ ከመንደሩ ፡ የሚመጣ ፡ ሰው ፡ አገኘና ፡ "እንዴት ፡ዋሉ ፡ ጌታ ?" አለ ።

"እግዚአብሄር ፡ ይመስገን ፡ እንደምን ፡ ዋሉ ?" አለ ፡ መንደረኛው ።

"እባክዎ ፡ የኔ ፡ ጌታ ፡ ዲማ ፡ ከዚህ ፡ ብዙ ፡ ያስሄዳል? "

" ደርሰዋል ፡ "

" ከዚህ ፡ ከመንደሩ ፡ ወዴት ፡ ነው ?"

" ከየትኛው ፡ መንደር ?"

" እዚህ ፡ እፊቴ ፡ ከማየው ፡ " አለ ፡ በዛብህ ፡ አገጩን ፡ ወደ ፡ መንደሩ ፡ አሾሎ ፡

" ሙሉ ፡ ጠቢያ ፡ የሚያከብረውን ፡ ደብር ፡ እርስዎ ፡ መን

